በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

# የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

## ቁጥር 760/2013

ጥቅምት 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**መግቢያ**

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የበርካታ ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች ባለቤት አገር ነች፡፡ ይህ ባህላዊ ብዝሀነትና ህዝቦቿ በረጅም ዘመናት ያፈሯቸው ቅርሶች ለሀገሪቱ ሰፊ የሀብትና የልማት መሠረት ሆነው ሊያገግሉ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ቅርሶች የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ የአለፈው ትውልድ የታሪክና የሥልጣኔ አሻራ፤ የአሁኑ ትውልድ የልማትና የብልጽግና መገለጫ፤ የተተኪው ትውልድ ደግሞ አለኝታና ተስፋ ሆነው እንዲገኙ ይጠበቃል፡፡

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ለአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ባህልና ቅርስ አስፈላጊውን የህግ ከለላ ሰጥቶ ይገኛል፡፡ ይህም ሰኔ 20 ቀን 1992 ዓ.ም. በወጣ ነጋሪት ጋዜጣ የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ተብሎ በቁጥር 209/2000 በፀደቀ ህግ ተደንግጐአል፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲጠገኑና አስፈላጊው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ለሀገር ልማት እንዲውሉ የተመቻቸበት ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡

ይህ ዓዋጅ የቅርስ ዓይነቶች፣ የቅርሶች የባለቤትነት ይዞታ፣ የቅርስ ጥናትና ምርምር፣ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ የመሳሰሉ አበይት ጉዳዮች የሕግ ማዕቀፍ እንዲያገኙ የተደረገበት ነው፡፡ በዚሁ አዋጅም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባርም በክፍል አንድ፣ በአንቀጽ 6 ላይ በግልጽ ተደንግጐ ይገኛል፡፡

በአዋጁ ላይ እንደጠቀሰው ቅርሶች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ፣ ግዝፈትነት ያላቸውና ግዝፈትነት የሌላቸው በሚል ተፈርጀው ሠፊ ትርጓሜ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ የቅርስ ጥናትና ምርምሩ ይዘትም በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ በምድርና በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ቅርሶች ላይ፣ በአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ላይ ብሎም በተለያየ ምክንያት ከአገር የወጡ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የሚደረጉ ዘርፈ ብዙ የጥናትና ምርምር መስኮችን የሚያካትት መሆኑ ተገልጿል፡፡

ባለሥልጣን መ/ቤቱም በዚህ ዓዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ይህ የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሠጣጥ መመሪያ እንዲወጣ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ይህ መመሪያ በዚህ አዋጅ መሠረት በአንቀጽ 32 የተመለከተውን ተመርኩዞ የወጣ ዝርዝር የአዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ነው፡፡

FINAL DRAFT

FINAL DRAFT

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>

**1. አውጭው ባለሥልጣን፣**

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**2. አጭር ርዕስ፣**

ይህ መመሪያ "የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 760/2013 ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3. ትርጓሜ**

በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/92 የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ከዚህ በተጨማሪ፡-

1. "የቅርስ ጥናትና ምርምር" ማለት ቅርሶችን መፈለግ፣ ማግኘት፣ መለየት፣ ዶክመንት ማድረግ፣ እና ለሕትመት ማብቃት ነው፡፡
2. "ተመራማሪ" ማለት በግሉ ወይም በአንድ የተመራማሪዎች ቡድን ውስጥ ታቅፎ በሰለጠነበት የሞያ ዘርፍ ምርምር የሚያካሂድ ባለሞያ ነው፡፡
3. "የቡድን መሪ" ማለት በአንድ የተመራማሪዎች ቡድን የሚካሄድን የቅርስ ጥናትና ምርምር ተግባርን በበላይነት የሚመራ ባለሞያ ነው፡፡
4. "የጥናትና ምርምር ቡድን" ማለት ሁለትና ከዛ በላይ አባላት ያሉት የጥናትና ምርምር  የባለሞያዎች ስብስብ ማለት ነው፡፡
5. "የጥናትና ምርምር ፈቃድ" ማለት ለቅርስ ፍለጋ፣ ግኝት፣ እንዲሁም ለማህበረሰብ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ላመለከቱ የተመራማሪዎች /ቡድን/ በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 30 መሠረት በጽሑፍ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
6. "የቅርስ አድን ፈቃድ" ማለት በግንባታና ሌሎች የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራ ምክንያት ወይም በተፈጥሮ ክስተቶች ለአደጋ የተጋለጡ ቅርሶችን በአፋጣኝ ለማዳን በባለሥልጣኑ ወይም በሌሎች ጠያቂዎች አማካይነት ሞያዊ ብቃቱና የገንዘብ አቅሙ ላላቸው አካላት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
7. "የአገር ውስጥ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጥናት ፈቃድ" ማለት ለኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ለሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆን በኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ጥናት እንዲያደርጉ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
8. "የጥናት ቦታ ወሰን" ማለት ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን ጥናት እንዲያካሂድ የሚፈቀድ የቦታ መጠነ ሥፋት ልክ ነው፡፡
9. "የመስክ ጥናትና ምርምር ክፍያ" ማለት አንድ ተመራማሪ ወይም የጥናት ቡድን ለጥናትና ምርምሩ ከሚያገኘው የገንዘብ መጠን ውስጥ በመቶኛ ተሠልቶ ለባለስልጣኑ መ/ቤት የሚፈፅመው ክፍያ ነው፡፡

10. "የጥናትና ምርምር ውጤት ሕትመት" ማለት ስለ ቅርሶች ግኝትና ጥናት በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል የሚችል መረጃ የያዘ፣ ተገምግመው በሚታተሙ ሳይንሳዊ መጽሔቶች፣ በሞኖግራፍ፣ በመጻሕፍትና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ላይ የሚወጣ ጥናታዊ ጽሑፍ ወይም አጠቃላይ የቅርሶችን አገኛኘት፣ ይዘትና ዝርዝር ጥናት የሚያካትት ህትመት ማለት ነው፡፡

11. "የጥናት የምርምር ፈቃድ ዘመን" ማለት በቅርሶች ላይ እንደ ምርምር ዘርፉ ዓይነትና ስፋት ምርምር ለማድረግ ለሦስት ዓመት ጊዜ ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን የሚሰጥ የጥናት ፈቃድ ዘመን ነው፡፡

12. "የፈቃድ ዓመት" ማለት ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን በፍቃድ ዘመን ውስጥ በየዓመቱ የሚታደስ ሆኖ ለአንድ ዓመት የሚሰጥ የፈቃድ ጊዜ ነው፡፡

13. "የጥናት የምርምር ማመልከቻ" ማለት ጥናትና ምርምር የማድረግ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የምርምር ዘርፎች

### 4. በመስክ ላይ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥናትና ምርምር ዘርፎች

1. የፓሊዮአንቶሎጂ ጥናት
2. የፓሊዩአንትሮፖሎጂ ጥናት
3. የአርኪዎሎጂ ጥናት
4. የአንትሮፖሎጂ ጥናት

### 5. ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ልዩ ልዩ ተግባራት

1. የቅርስ አድን ጥናት
2. በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስልጠና
3. መስክ ላይ የሚገኙ የተንቀሳቃሽና የቋሚ ቅርሶች ጥናት

FINAL DRAFT

## ክፍል ሦስት

## የፈቃድ ማመልከቻ ይዘት

6. **የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ይዘት**

1. የጥናትና ምርምር ቡድን መሪዎችና አባላት ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣
2. የሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ኮፒ፣
3. የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ (Curriculum Vitae)፣
4. የሚሰሩበት ወይም የሚማሩበት ተቋም ስምና ሙሉ አድራሻ እንዲሁም የተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ፣
5. ስለ ቡድን መሪው /መሪዎች/ ምሥክርነት ሊሰጡ የሚችሉ ጥናቱ በሚካሄድበት ዘርፍ በምርምር ሥራዎቻቸው የታወቁ ሦስት ባለሙያዎች ስምና ሙሉ አድራሻ፣
6. የጥናቱ ርዕስ፣
7. የጥናቱ መስክ፣
8. ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ፣
9. የመስክ ጥናቱ የሚከናወንበት ጊዜ (ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት)፣
10. ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ የቦታው ልዩ መጠሪያ፣
11. ጥናቱ የሚካሄድበት ሥፍራ መጠን /የቦታ ሥፋት/ በኢትዮጵያ የካርታ ሥራ ኤጀንሲ በ1፡50,000 መጠን የተዘጋጀ ቶፖግራፊክ ካርታ እና ከሳተላይት የተነሱ ምስሎች (High accuracy Satellite Imagery) አያይዞ ማቅረብ፣
12. በጥናቱ ሂደት የሚመለሱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና መላምቶች፣
13. የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚጠቀምባቸው የጥናት ሥልቶች (methods)፣
14. ተመራማሪው ጥናቱን ለማካሄድ በመስክ የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች፣
15. ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ምንጭ፣
16. ጥናቱን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የተጠየቀበት ፕሮፖዛል ኮፒ፣
17. የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው ድርጅት /ተቋም/ ገንዘቡን መስጠቱንና የተገኘውን ገንዘብ መጠን የሚገልጽ መረጃ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፣

FINAL DRAFT

## 7. የጥናትና ምርምር ጥያቄ አቀራረብና ሂደት

1. አንድ ተመራማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናት የምርምር ጥያቄ ሲያቀርብ ስለሚያጠናው ጉዳይ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ፍሬ ጉዳዩን (concept note) የሚያስረዳ ማመልከቻ ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት በአካል በመገኘት ወይም በባለሥልጣኑ አድራሻ ወደ መስክ ለመሄድ ከታቀደው ጊዜ ሁለት ወር ቀደም ብሎ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

2. ባለሥልጣኑ የጥናቱን አስፈላጊነት በመገምገምና ለጥናት የተጠየቀው ቦታ ከዚህ ቀደም በሌሎች ተመራማሪዎች ያልተያዘ መሆኑን በማረጋገጥ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡

3. በተራ ቁጥር 2 የቀረበው የጥናትና ምርምር ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያገኝ የጥናት ማመልከቻ ክፍያ፣ በብሔራዊ ባንክ በኩል፤

   3.1 የውጭ ዜጋ የሆነ ተመራማሪና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች በአሜሪካን ዶላር 50፣

   3.2 በውጪ አገር ትምህርቱን የሚከታተል ኢትዮጵያዊ ተማሪ በአሜሪካን ዶላር 25፣

   3.3 በአገር ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ከሚማሩበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ካመጡ ከክፍያ ነፃ የሆነ አገልግሎት ያገኛሉ፣

   3.4 ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ ሆኖ የገንዘብ ምንጩ ከውጪ ከሆነ በተ.ቁ. 3.1 የተመለከተውን ክፍያ ይፈጽማል፣

   3.5 ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ ሆኖ ምንጩ ከአገር ውስጥ ከሆነ ከሚመለከተው ድጋፍ ሰጪ አካል የድጋፍ ደብዳቤ ካቀረበ ከክፍያ ነፃ የሆነ አገልግሎት ያገኛል፣

4. አመልካቹ የጥናት ማመልከቻ ክፍያ መክፈሉ ሲረጋገጥ የጥናት መጠየቂያ ቅጹ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

5. የጥናት ፈቃድ ጠያቂው ከላይ የተጠቀሱትን ካሟላ በኋላ ቅጹንና ክፍያ የፈጸመበትን ደረሰኝ ወይም የሚመለከተውን የድጋፍ ደብዳቤ ከአስፈላጊው መረጃዎች ጋር በማያያዝ በመዝገብ ቤት በኩል ለባለስልጣኑ መ/ቤት ገቢ ያደርጋል፣

6. የሚቀርበው የጥናትና ምርምር ማመልከቻ በመዝገብ ቤት ከተመዘገበ በኋላ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ለግምገማ ወደ ቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ይላካል፡፡

## 8. የአርኪዎሎጂ፣ የፓሊዮንቶሎጂና የፓሊዮ-አንትሮፖሎጂ የጥናት መስኮች የጥናት ፈቃድ ማመልከቻ የመገምገሚያ ነጥቦች

1. የጥናትና ምርምር ቡድኑ መሪና አባላት የትምህርት ዝግጅትና ብቃት እንዲሁም የምርምር ልምድ ሊካሄድ ከታቀደው ጥናትና ምርምር ዓይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑ፣

2. የጥናትና ምርምር ቡድን መሪው የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ እና በመስኩ የሥራ ልምድ ያለው እንዲሁም ሶስት ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የመስኩ ባለሙያዎች ስምና አድራሻ ያቀረበ መሆኑ፣

FINAL DRAFT

3. ከኢትዮጵያዊያን የቡድኑ አባላት፣ ልዩ ሙያ ካላቸውና የቴክኒክ ድጋፎችን ከሚሰጡ ባለሙያዎች እንዲሁም በመስኩ የፒ.ኤች.ዲ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ የውጭ ዜጋ ተማሪዎች በስተቀር ሌሎች የቡድን አባላት ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፣

4. የቡድኑ አባላት ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሙያውን ሥነ-ምግባር የሚጻረር ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑ፣

5. ለመስክ ጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችና መሣሪያዎች አሟልተው መገኘት፣

6. የሚቀርበው የጥናት ሥልት ቡድኑ ካለው የጥናት መሣሪያዎችና ከአባላቱ ሙያና እውቀት ጋር መጣጣም፣

7. ቡድኑ ጥናቱን ለማካሄድ ያገኘው የገንዘብ መጠን ከአባላቱ ብዛት፣ ከጥናቱ ዓይነት፣ በመስክ ከሚቆይበት ጊዜና ከተፈቀደለት መካነ ቅርስ ስፋት አንፃር በቂ ሆኖ መገኘት፣

8. የጥናትና ምርምር ቡድኑ ከመስክ ለሚያሰባስባቸው ቅርሶች በቂ እና ደረጃውን የጠበቀ ማከማቻ ካቢኔቶችና መደርደሪያዎችን ማሟላቱ፣

9. የጥናትና ምርምር ቡድኑ የባለስልጣን መ/ቤቱ የሚመድብለትን ኢትዮጵያውያን የቅርስ ምርምር ባለሙያዎችን በምርምር ሥራ ውስጥ የሚያሳትፍና አቅም የሚገነባ መሆኑ፣

10. ጥናቱን በሚያካሂድበት ቦታ ለአደጋ የተጋለጡ ቅርሶች ላይ ጥንቃቄ የማድረግና የማዳን ኃላፊነት የሚወስድ መሆኑ፣

## ክፍል አራት

## ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

### 9. የጥናትና ምርምር ፈቃድ ግምገማና አሰጣጥ

1. የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተመዝግቦ የቀረበውን የጥናትና ምርምር ፈቃድ ማመልከቻ ለሚመለከተው ባለሙያ ለግምገማ ይመራል፡፡

2. ማመልከቻ የቀረበለት ባለሙያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተጠቀሱት ነጥቦች መሠረት የጥናትና ምርምር ማመልከቻውን ይዘት ገምግሞ ውጤቱን በአንድ ቀን ውስጥ ያሳውቃል፡፡

3. በፅሁፍ ለቅርስ ፍለጋ ግኝትና ጥናት የሚሰጥ ፈቃድ የአመልካቹን ስም፣የጥናትና ምርምር ቡድኑ ስም፣ የጥናቱ ርዕስ፣ ፈቃድ የተጠየቀበትና የተሰጠበትን ቀን፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን የጥናት መስክ፣ ጥናቱ የሚካሄድበትን ቦታ /ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ/፣ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስም ፊርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡

4. ለግምገማ የቀረበ ማመልከቻ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው ተመራማሪ /ቡድን መሪ/ መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በዳይሬክቶሬቱ ጽ/ቤት በኩል ይገለጽለታል፡፡ ምላሽ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠይቁን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡



FINAL DRAFT

5. ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ፈቃድ የተሰጠው ተመራማሪ /የጥናት ምርምር ቡድን/ ፈቃድ ካገኘ በኋላ አቅርቦት በነበረው የጥናት ማመልከቻ መሠረት ጥናቱን በትክክል ስለማከናወኑ በሚቀርቡ የመስክ ሪፖርቶች ተገምግሞ ሲረጋገጥ በየዓመቱ የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ ፈቃዱ ይታደሳል፡፡

## 10. በአርኪዎሎጂ፣ በፓሊዮንቶሎጂ እና ፓሊዮ አንትሮፖሎጂ የሚፈቀደው የጥናት ቦታ መጠን

1. በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1-3 ላይ ለተጠቀሱት የጥናት መስኮች የሚፈቀደው የቦታ መጠን የተያያዘና ያልተቆራረጠ ሆኖ ከ100 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ ይሆናል፡፡

2. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከ100 ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ ስፋት ያለው የጥናት ቦታ የተፈቀደላቸው የጥናትና ምርምር ቡድኖች በአዋጅ ቁጥር 209/92 አንቅጽ 33 ቁጥር 1 እና 2 በተፈቀደው መሠረት ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት እንዲይጠኑ የሚፈቀድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በኋላ ጥናታቸውን ለማራዘም በዚህ መመሪያ መሠረት በአዲስ መልክ ማመልከት ይገባቸው፡፡

3. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በንዑስ አንጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠቀሱት የጥናት መስኮች የቅድመ አሰሳ ባልተካሄደባቸው ቦታዎች አሰሳ ለማድረግ እና የጥናት ቦታ ለመምረጥ በአንድ የፈቃድ ዓመት የሚሰጠው የቦታ መጠን ከ100 ካሬ ኪሎ ሜትር ሊበልጥ ይችላል፡፡

4. የቅድመ አሰሳ ጥናት በሚከናወንበት ጊዜ የጥናት ቦታ ከመምረጥ ውጪ ምንም ዓይነት የቅርስ ማሰባሰብም ሆነ የቁፋሮ ተግባር ማከናወን አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን የጥናት ቦታ በሚመርጥበት ጊዜ ቅርሱ አደጋ የሚደርስበት ሆኖ ካገኘው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ተወካይ ጋር የተገኘውን ቅርስ በመመዝገብ ወደሚመለከተው የቅርስ ክምችት ቦታ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይኸ ቅርስ በኋላ ቅርሱ የተገኘበትን ቦታ እንዲያጠና ለተፈቀደለት የጥናት ፕሮጀክት ተሰጥቶ እንዲጠና ይደረጋል፡፡

5. አንድ ነባር ተመራማሪ አዲስ የጥናት ቦታ ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብ ቀደም ሲል በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናትና ምርምር ማጠናቀቁ፣ ከመስክ ላሰባሰባቸው ቅርሶች ተገቢውን እንክብካቤና ምዝገባ ማከናወኑ፣ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በቂ መረጃ የሚሰጡ ሳይንሳዊ ጽሑፎችን ማሳተሙ፣ የጥናትና ምርምር ሥራውን በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ማከናወኑና ለባለሥልጣኑ የአቅም ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረጉ ተረጋግጦ ይሆናል፡፡

## 11. ለጥናት የሚፈቀድ ጊዜ

1. አዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀጽ 33 እንደተጠበቀ ሆኖ ጥናቱ በተፈቀደው የጥናት ዘመን ውስጥ ካልተጠናቀቀ ተመራማሪው የጥናት ጊዜው እንዲራዘምለት ማመልከቻ ሲያቀርብ በቅድሚያ በሰራበት የጥናት ዘመን ያሰባሰባቸውን ቅርሶች መረጃ በአግባቡ ማጠናቀቁና የኪዩሬሽን ሥራ ማጠናቀቁ ተረጋግጦ ለቀጣዩ ሁለት ዓመት ሊራዘምለት ይችላል፡፡

2. የፈቃድ ዘመኑን ላጠናቀቀና በአዲስ መልክ የፈቃድ ማመልከቻ የሚያቀርብ የጥናትና ምርምር ቡድን በቅድሚያ በተሰጠው የፈቃድ ዘመን ያሳተማቸው የምርምር ሕትመት ውጤቶች ለሳይንስና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ያበረከተው አስተዋጽኦ፣ ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ያበረከተው ድርሻ እንዲሁም ያሰባሰባቸውን ቅርሶች

FINAL DRAFT

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚያቀርበው ፎርማት ዶክሜንት ማድረጉና የኪዩሬሽን ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ ማከናወኑ ተረጋግጦ ይሆናል፡፡

**12. የኢንታንጀብልና የሶሻል አንትሮፖሎጂ ጥናት ፕሮፖዛል የመገምገሚያ ነጥቦች**

1. ማንኛውም በዚህ መስክ ጥናትና ምርምር ለማከናወን ጥያቄ የሚያቀርብ ተመራማሪ ወይም የጥናት ቡድን መሪ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያለውና በማመልከቻው ካቀረበው የጥናትና ምርምር ጥያቄ አኳያ ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው መሆኑ፣
2. የጥናቱ ርዕስ መጠቀሱን፣
3. ጥናቱ የሚካሄድበት ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ እንዲሁም ክልል መጠቀሱ
4. ጥናቱ የሚካሄድበትን ልዩ ሥፍራ (research site)፣
5. የጥናቱ ዓላማ፣ አስፈላጊነትና ግብ፣
6. በጥናቱ መልስ ሊሰጣቸው /ሊመለሱ/ የታሰቡ የምርምር ጥያቄዎች (research questions)፣
7. የጥናትና ምርምሩ ዘዴ (research methodology)፣
8. ለጥናቱ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት፣
9. ጥናቱ የሚወስደውን ጊዜና ክንውኖችን የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ፡፡
10. በጥናት ወቅት አጥኚው የሚከተላቸው የሙያ ሥነ ምግባሮች (ethical issues) ያለው መሆኑ፡፡

**13. የድህረ ምረቃ ማሟያ ጥናታቸውን በኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ለሚያካሂዱ ተማሪዎች የጥናት ፕሮፖዛል ጥያቄ መገምገሚያ ነጥቦችና ፈቃድ አሰጣጥ**

1. የአማካሪ መምህር ስም፣ የትምህርት ተቋም ስም፣ የሚከታተሉትን የትምህርት ዓይነት፣ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ርዕስ፣ የጥናቱ ስልት፣ ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ፣ ለፕሮጀክቱ ማስኬጃ የሚያገኙትን የገንዘብ መጠን በጥናት ጥያቄቸው ላይ መካተት ይኖርበታል፡፡
2. የቀረበው የጥናት ጥያቄ ማመልከቻ አመልካቹ ከሚከታተለው የትምህርት ዘርፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የተማሪው አማካሪ በመስኩ የሠለጠነና በቂ ልምድ ያካበተ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡
4. ተማሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4-8 ያሉትን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡
5. የተማሪውን የጥናትና ምርምር ጥያቄ አቀራረብ በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1-6 በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡
6. ለጥናቱ የሚሰጠው የፈቃድ ጊዜ ለሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተማሪው ከአቅሙ በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ጥናቱን ቢያቋርጥና እንደገና ለመቀጠል ቢፈልግ ከሚማርበት ተቋም ያቋረጠበትን ምክንያት በበቂ ማስረጃ ካቀረበ

FINAL DRAFT

የጥናት ጊዜው ለአንድ ዓመት ሊራዘምለት ይችላል፡፡ ነገር ግን የፒኤችዲ ዲግሪ ተማሪ ከሆነ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥናቱን ካላጠናቀቀ ለ2 ዓመት ጊዜ ሊራዘምለት ይችላል፡፡

7. ተማሪው ለጥናቱ የተፈቀደለት ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቦታው ለአንድ ዓመት ለሌላ አጥኚ አይሰጥም፡፡ ነገር ግን የአንድ ዓመት የጊዜ ገደቡ ካበቃ በኋላ ተማሪው ቀጣይ ጥናት ማድረግ ከፈለገ ከሌሎች አጥኚዎች ቅድሚያ ለማግኘት በቅድሚያ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

8. በፓሊዮንቶሎጂ፣ በአርኪዎሎጂ እና በፓሊዮ አንትሮፖሎጂ የጥናት መስኮች ተማሪው በመስክ የቁፋሮ ጥናት ለማካሄድ የሚችለው ከአማካሪ መምህሩና የባለሥልጣኑ ተወካይ ባሉበት ብቻ ይሆናል፡፡

9. ተማሪው ኢትዮጵያዊ ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 7፣ 8፣ 10 ፣ እና 12 ከተጠቀሱት ግዴታዎች በስተቀር ሌሎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለቅርስ እድን ፈቃድ</u>

**14. የቅርስ አድን ለማከናወን ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በመስኩ የሚሠማሩ ተመራማሪዎች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

1. በዘርፉ በቂ ሙያና ልምድ ያላቸውና፣ በተለያዩና ተዛማጅነት ካላቸው የሞያ ዘርፎች የሰለጡኑ ባለሙያዎችን ማካተት፣
2. በቂ የፋይናንስና የሎጂስቲክ አቅም መኖር፣
3. የቅርስ ማዳንና ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ማመላከት፣
4. በመስኩ የሰለጠኑ የባለሥልጣኑንና የቅርስ አድን ሥራው የሚካሄድበትን ክልል ባለሞያዎችን በሥራው ላይ ማሳተፍ፣
5. ሥራው የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ማመላከት፡፡

FINAL DRAFT

FINAL DRAFT

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>*የተመራማሪዎች መብትና ግዴታ*</u>

### 15. *የተመራማሪው መብቶች*

1. አንድ ኢትዮጵያዊ የጥናትና ምርምር የቡድን መሪ ከሆነ ከሚመራው የጥናት ቡድን በተጨማሪ በሌሎች ሁለት የጥናትና ምርምር ቡድኖች ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ይችላል፡፡ የጥናትና ምርምር ቡድን መሪ ካልሆነ ግን በሦስት የጥናት ቡድኖች በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ ቡድን ውስጥ በአባልነት እንደሚሳተፍ ቀደም ብሎ ለነበረበት ቡድን መሪ ተሳትፎውን ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡
2. አንድ የውጭ ዜጋ የጥናትና ምርምር ቡድን መሪ ከሆነ በአንድ ተጨማሪ የጥናትና ምርምር ቡድን ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ይችላል፡፡ የጥናትና ምርምር ቡድን መሪ ካልሆነ ግን በሁለት የጥናትና ምርምር ቡድኖች በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል፡፡ የተለየ የቴክኒክ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎችን በተመለከተ ግን በባለሥልጣኑ መ/ቤት ታይቶ ይፈቀድላቸዋል፡፡
3. አንድ ተመራማሪ በተሰጠው የጥናት ፈቃድ ዘመን ውስጥ ከመስክ ባሰባሰባቸው ቅርሶች ላይ ያደረገውን የጥናት ውጤት የማሳተም ብቸኛ ባለመብት ይሆናል፡፡
4. ተመራማሪው በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች የጥናት ፈቃድ እድሳት ሳያደርግ ቢቀር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለአንድ ዓመት ጊዜ ብቻ የተሰጠውን የጥናት ቦታ ለሌላ አጥኚ አሳልፎ ሳይሰጥ ሊጠብቀው ይችላል፡፡
5. በባለሥልጣኑ የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የፈቃድ ዘመኑን ያላጠናቀቀ የጥናትና ምርምር ቡድን ለጥናት በተፈቀደለት መካነ ቅርስም ሆነ ከመስክ ባሰባሰባቸው ቅርሶች ላይ ካለ ቡድኑ ዕውቅናና ፈቃድ በሦስተኛ ወገን ምንም ዓይነት ጥናትና ምርምር እንዳይካሄድበት ይደረጋል፡፡

### 16. *የተመራማሪው ግዴታዎች*

1. ማንኛውም የጥናትና ምርምር ቡድን በማመልከቻው ቅጽ ላይ የሚሞላቸው መረጃዎችና ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማናቸውም ማስረጃዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉና ጽሑፎቹም የተተየቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. የቅርስ ጥናትና ምርምር የፈቃድ እድሳት ጥያቄ የመስክ ጥናቱ ከመጀመሩ ከ2 ወር በፊት በኢሜል በፋክስ በግንባር ቀርቦ ወይም በፖስታ በመላክ ለቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት፡፡ አዲስ የቅርስ ጥናትና ምርምር የፍቃድ ጥያቄ ማመልከቻ በግንባር ወይም በፖስታ መላክ ይኖርበታል፡፡
3. ከአንድ ዓመት በላይ በመስክ የሚካሄድ የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
4. አንድ የጥናትና ምርምር ቡድን የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የመስክ ሥራውን ፍቃዱ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥናቱን መጀመር ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥናቱን ካልጀመረ የተሰጠው የጥናት ፈቃድ ይሠረዛል፡፡

5. ማንኛውም ተመራማሪ ጥናትና ምርምሩን ለማካሄድ ያገኘውን የገንዘብ መጠን፣ የተሰጠበት የገንዘብ ዓይነት (currency) እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ እንደተሰጠው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ገንዘቡን ካገኘበት ተቋም ማቅረብና ወደ ሀገር የሚያስገባቸውን ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ለባለሥልጣኑ ማስመዝገብ አለበት፡፡

6. በአንቀፅ 7 ተራ ቁጥር 3 በተጠቀሰው መሠረት ተመራማሪው ለጥናትና ምርምር ማመልከቻ ክፍያ መፈጸምና ደረሰኙን ከማመልከቻው ጋር ማያያዝ አለበት፡፡

7. የውጭ ዜጋ የሆነ ተመራማሪ እና በውጭ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ ለመስክ ጥናትና ምርምር ሥራ ተብሎ ከሚያገኘው አጠቃላይ ገንዘብ የጥናትና ምርምር አገልግሎት ክፍያ 10% በአሜሪካን ዶላር ወይም በዩሮ መስክ ከመውጣቱ በፊት መክፈል አለበት፡፡

8. በሀገር ውስጥ በሚገኝ የትምህርት ወይም የጥናትና ምርምር ተቋም የሚሠራ ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ የገንዘብ ምንጩ ከውጭ ወይም ከሀገር ውስጥ የግል ተቋማት ከሆነ ከሚያገኘውና ለመስክ ሥራ ተብሎ ከተያዘው አጠቃላይ ገንዘብ 5% የጥናት ክፍያ በኢትዮጵያ ብር ይከፍላል፡፡

9. ማንኛውም የጥናት ማመልከቻ ክፍያም ሆነ የጥናትና ምርምር ክፍያ ሲፈጸም በደረሰኙ ላይ የጥናትና ምርምር ቡድኑ ስም መጠቀስ አለበት፡፡

10. በቂና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር ለአንድ የጥናት ዓመት የተከፈለ ማመልከቻም ሆነ የጥናትና ምርምር ክፍያ የሚያገለግለው ጥናቱ ይካሄዳል ተብሎ ለተጠየቀበት ዓመት ብቻ ነው፡፡

11. ማንኛውም የጥናትና ምርምር ቡድን የባለሥልጣኑንና ጥናቱ ከሚካሄድበት ክልል ተወካይ ይዞ ወደ መስክ መንቀሳቀስ አለበት፡፡ እነዚህ ተወካዮች በመስክ ሥራ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ የምግብና የመኝታ ወጪን የመሸፈንና በቀን 25 የአሜሪካን ዶላር በወቅቱ በሚኖረው የኢትዮጵያ ብር ምንዛሪ የውሎ አበል መክፈል አለበት፡፡ ለተወካዮቹና ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የጥናትና ምርምር ቡድን አባላት የ24 ሰዓት የመድን ዋስትና መግባት አለበት፡፡

12. በአንድ የፈቃድ ዘመን ውስጥ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ወይም ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በባለሥልጣኑ ውሳኔ መሰረት የሚመደብለትን አንድ የቅርስ ባለሙያ በረዥም ጊዜ ትምህርት ያሰለጥናል፡፡

13. ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ወግ፣ ባህልና እምነት ማክበር አለበት፡፡

14. ተመራማሪው ከመ/ቤቱ ተወካይና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ያለው የዕለት ተዕለት የሥራ ግንኙነት ሥነ ምግባርን የተላበሰና ከበሬታ የተሞላው ሊሆን ይገባል፡፡

15. በጥናትና ምርምር ማመልከቻ ስማቸው ያልተጠቀሱ አባላትን ወይም ባለሥልጣኑ ሳያውቀውና በጽሑፍ ሳይፈቀድ በጥናቱ ውስጥ ማሳተፍ አይቻልም፡፡

16. በቅርሶችና በመካነ ቅርሶች ላይ አደጋ ሊያመጣ ከሚችል አሠራር መታቀብ አለበት፡፡

17. አንድ ተመራማሪ እንዲያጠና በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናት በተፈቀደለት የጥናት ጊዜ ገደብ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት፡፡

FINAL DRAFT

18. ለቅርሶች ደህንነት ሲባል በመስክ የሚከናወን የቅርስ ፍለጋና የቁፋሮ ጥናት ከቀኑ 12 ሰዓት በኋላ ያለማከናወን እንዲሁም የመስክ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ ግኝቶች ወደ ባለሥልጣኑ መ/ቤት በሚጓጓዙበት ወቅት ከ12 ሰዓት በኋላ ማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡

19. አንድ የጥናትና ምርምር ቡድን የዓመቱን የመስክ ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ የመስክ ሥራ ሪፖርት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

20. አንድ የጥናትና ምርምር ቡድን በመስክ ሥራ ላይ የሚያከናውናቸውን የቁፋሮ ጥናት ሥራዎች አስመልክቶ በየዓመቱ ከሚያቀርባቸው ሪፖርቶች በተጨማሪ የቁፋሮውን ሂደት የሚያመላክት ፕላንና ቅርሶች እንዴት እንደተገኙ የሚይሳይ ሙሉ ዘገባ (Progress report) ቁፋሮው ከተጠናቀቀ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አጠናቅሮ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ የጥናትና ምርምር ፈቃድ ዘመኑ ሥራ ሲጠናቀቅ ከሚቀርበው የመጨረሻ የሥራ ሪፖርት ጋር ምርምር የተደረገባቸው ቦታዎች እና ዋና ዋና የግኝት ቦታዎችን የሚያመላክቱ የአየር ፎቶግራፎች፣ የቶፖግራፊክ ካርታዎችና የጂፒኤስ መረጃዎች ተካተው ለባለሥልጣኑ መ/ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡

21. የቁፋሮ ጥናት የተካሄደባቸውን ቦታዎች ለቀጣይ ጥናት ማመቻቸት እንዲሁም የቁፋሮ ጥናት የተጠናቀቀባቸው ቦታዎችን ቀድሞ ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ አለበት፡፡

22. ተመራማሪው ከመስክ የሚያገኛቸውን ቅርሶች ተንከባክቦና በሥርዓት መዝግቦ በቂና ደረጃቸውን የጠበቁ ማከማቻ ቁሳቁሶችን አሟልቶ ማስቀመጥ አለበት፡፡

23. ማንኛውም የጥናትና ምርምር ቡድን ከመስክ ያሰባሰባቸውን ቅሪተ አካላትና ሌሎችንም ቅርሶች በአግባቡ አጽድቶና አዘጋጅቶ ለቀጣዩ ጥናት በሚያመች መልኩ ማዘጋጀት አለበት፡፡

24. የግብረ ሕንፃዎች ፍርስራሽ፣ ቅሪቶቻቸው የማይንቀሳቀሱ ቅርሶችና ትክል ሐውልቶችን ማንቀሳቀስ አይቻልም፡፡

25. ለመካነ ቅርሶች ስያሜ ኢትዮጵያዊ፣ እንዲሁም ለቅርሶቹ ሳይንሳዊ ይዘት ያለው ኢትዮጵያዊ ሥያሜ መስጠት፡አለበት፡፡

26. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የቅርስ ናሙናዎችን ከሀገር ለማስወጣት የባለሥልጣኑን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

27. በመስክ ጥናትና ምርምር ወቅት በተገኙ ቅርሶች ላይ በሌላ አካል ጋዜጣዊ መግለጫ /ፕሬስ ሪሊዝ/ ከመስጠቱ በፊት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

28. ካሳተማቸው የጥናት ውጤቶች አምስት ኦሪጅናል ቅጂዎችን ለባለሥልጣኑ መስጠት አለበት፡፡

29. ማንኛውም የውጭ ዜጋ የሆነ ተመራማሪ ለመስክ ሥራ ከአዲስ አበባ ከመውጣቱ በፊት የፓስፖርት ኮፒውን ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

30. ለባለሥልጣኑ የሚቀርቡ ሪፖርቶች፣የጥናት ዶክመንቶችና የህትመት ውጤቶች በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጁ ከሆነ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው፡፡

31. የቅርስ ጥናትና ምርምር ሥራ እና የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራን ጐን ለጐን የሚያካሄዱ ተመራማሪዎች በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 16 እና 17 ላይ የተቀመጡትን የጥናት ፈቃድ ማመልከቻ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

FINAL DRAFT

## ክፍል ሰባት

## በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስልጠና

**17. በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ሥልጠና ማመልከቻ ይዘትና መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

1. በመስክ ላይ ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኝ መምህራን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣
2. የሠልጣኝ ተማሪዎች ብዛትና የስም ዝርዝር እንዲሁም የትምህርት ደረጃ፣
3. መምህራኑ የሠለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ኮፒ ፣
4. የአሠልጣኝ መምህራንና የተማሪዎች የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ማስረጃ፣
5. አሠልጣኝ መምህራኑ የሚሠሩበት ተቋም ስምና ሙሉ አድራሻና የተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ፣
6. ስለ መምህራኑ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉና ሥልጠናው በሚካሄድበት ዘርፍ በምርምር ሥራዎቻቸው የታወቁ ሦስት ባለሙያዎች ስምና ሙሉ አድራሻ፣
7. የመስክ ላይ ሥልጠና የሚሰጥባቸው የትምህርት መስኮች፣
8. የመስክ ላይ ሥልጠናው የሚከናወንበት ጊዜ /ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት/፣
9. ሥልጠናው የሚሰጥበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ፣
10. ሥልጠናው የሚሰጥበት ቦታ ልዩ መጠሪያ፣
11. ሥልጠናው የሚሰጥባቸው ዘዴዎች፣
12. ሥልጠናውን ለማካሄድ በመስክ የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች እንዲሁም በላብራቶሪዎች የሚጠቀምባቸውን የመሣሪያ ዓይነት፣ ብዛትና አጠቃቀም፣
13. ሥልጠናውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ምንጭ፣
14. ሥልጠናውን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የተጠየቀበት ፕሮፖዛል ኮፒ፣
15. ከመስክ ሠልጣኝ ተማሪዎች የተገኘ የገንዘብ መጠንና ዓይነት፣
16. የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው ድርጅት /ተቋም/ ገንዘቡን መስጠቱን ወይም ለመስጠት ቃል መግባቱንና የሚሰጥበትን የገንዘብ ዓይነት (currency) መጠን እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ ለመስጠት እንደተስማማ የሚያረጋግጥ ማስረጃ /ደብዳቤ/ ማቅረብ፣
17. በመስክ ላይ ሥልጠና ለማካሄድ የሚቀርብ ጥያቄ መገምገሚያ ነጥቦች በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1-10 በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡

FINAL DRAFT

## 18. በመስክ ሥልጠና ለሚሳተፉ የተቀመጡ ግዴታዎች

1. በአንቀጽ 16 የተጠቀሱት የተመራማሪዎች ግዴታ በቡድን መሪውና በአሠልጣኝ መምህራን ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
2. በአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 13፣ 14፣ 16 እና 24 ላይ የተጠቀሱት ግዴታዎች በሰልጣኝ ተማሪዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ሠልጣኝ ተማሪዎች ማንኛውንም ቅርስም ሆነ የቅርስ ናሙና ከሀገር ለማስወጣት አይፈቀድላቸውም፡፡
3. በመስክ ከሚሰለጥኑት ተማሪዎች ከ20% ያላነሱ ኢትዮጵያውያንን የሚያሳትፍ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም የሰልጣኞቹ ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ ቢያንስ ከእነዚህ ሠልጣኞች መካከል አንዱ ሰልጣኝ ኢትዮጵያዊ ይሆናል፡፡ በዚህ ሥልጠና የመስክ ትምህርቱ ለሚካሄድበት ክልል ተሳታፊዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡
4. በመስክ ሥልጠና የሚወስዱ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከሀገር ውስጥ የትምህርት ተቋማት፣ ከክልል የባህል ቢሮዎችና ከባለስልጣን መ/ቤቱ ባለሙያዎች መካከል የመመልመል ኃላፊነት የባለሥልጣን መ/ቤቱ ይሆናል፡፡
5. አሠልጣኙ በሥልጠናው ለሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መጓጓዣ፣ ምግብ፣ መኝታና የመድን ዋስትና ይሸፍናል፡፡
6. ሥልጠናው የሚካሄደው ቀደም ሲል በተመራማሪዎች በተያዘና ጥናትና ምርምር በሚካሄድበት መካነ ቅርስ ላይ፣ እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለይቶ ለአሰልጣኞች በሚሰጣቸው መካነ ቅርስ ላይ እና ተመራማሪዎቹ ራሳቸው መርጠው ፈቃድ በሚጠይቁበት ቦታ ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡
7. በስልጠናው ላይ ለተሳተፉ ሠልጣኞች ስልጠናው ሲጠናቀቅ የምሥክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡
8. የባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቱ በሚገኙ የተመረጡ የፓሊዮአንትሮፖሎጂና የአርኪዎሎጂ መካነ ቅርስ ቦታዎችን ለመስክ ትምህርት ቤት (Field School) በየጊዜው እየሰየመ አገልግሎት እንዲሰጥባቸው ያደርጋል፡፡ አስፈላጊውን የክፍያ ተመንም በሂደት እንደወቅቱ ሁኔታ (Field season) እና በሚቀርቡለት ጥያቄ መሠረት እየተመነ ያሳውቃል፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱም በሚያሳውቀው ወቅታዊ ተመን መሠረት ተገልጋዮቹ ተገቢውን ክፍያ መፈጸም አለባቸው፡፡

FINAL DRAFT

<u>ክፍል ስምንት</u>

## 19. የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት

1. ለቅርስ ፍለጋ ግኝት ጥናትና ምርምር የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በተሟላ ሁኔታ ሲቀርቡ በአንድ ቀን ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የጥናትና ምርምር ሥራዎች በሀገሪቱ ሕግ መሠረት መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. የመጀመሪያው የሦስት ዓመት የጥናት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለተጨማሪ የሁለት ዓመት የጥናት ፈቃድ ዕድሳት ሲጠየቅ በተመራማሪው የሚቀርቡ የመሥክ ሥራ ሪፖርቶችና የጥናት ውጤቶች እንዲሁም የመ/ቤቱ ተወካይ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በመስክ ሥራ ወቅት በክልል የባህል ቢሮዎች፣ በመ/ቤቱ ተወካይ ወይም በተመራማሪዎች በሚቀርቡ ሪፖርቶች ውስጥ የተመለከቱ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን እንዲሁም የመመሪያ ጥሰቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. ለአሰሳና ለጥናት የሚፈቀደውን የመካነ ቅርስ ቦታ መጠን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት ይወስናል፡፡
6. ለጥናትና ምርምር የሚሰጠው ቦታ ቀደም ሲል ለሌሎች ተመራማሪዎች የተሰጡ የጥናት ቦታዎችን የማይነካ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
7. የተመራማሪውንና የመ/ቤቱን ተወካይ ሪፖርት በመገምገም የጥናቱን ሂደት የሚያመላክት ሪፖርት ለዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡
8. ተመራማሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 የተጣሉበትን ግዴታዎች ከጣሰና የሙያውን ዲሲፕሊን ካላከበረ የቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ዋና ዳይሬክተር በማሳወቅ በማናቸውም ጊዜ ፈቃዱን ሊያግድበት ይችላል፡፡ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምት የማይወስድና ጥፋቱ ከፍተኛ ሆኖ ከተገኘ ፍቃዱ እንዲሠረዝ ለመጨረሻ ውሳኔ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡
9. ከተመራማሪዎች ጋር በመስክ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ባለሙያ የሠለጠነበት የትምህርት ዓይነት አርኪዮሎጅ፣ ፓሊዮንቶሎጅ እና ፓሊዮ-አንትሮፖሎጅ መሆኑንና ከዚህ በፊት በመስክ ተመድቦ ሲሰራ ባለሙያው የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የተወጣና የሥነ ምግባር ጉድለት የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ይመድባል፡፡ ሆኖም ግን የተለየ የትምህርት ዝግጅት ለሚያስፈልጋቸው የጅኦሎጅ፣ ኮንሰርቬሽን እና የአንትሮፖሎጂ ጥናት ዘርፎች በጅኦሎጅ፣ ኮንሰርቬሽን እና አንትሮፖሎጂ የትምህርት አይነት የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ይመድባል፡፡

FINAL DRAFT

10. የተመራማሪዎችን ዝርዝር የያዘ የትብብር ደብዳቤ አዘጋጅቶ ጥናቱን ለሚያካሂድበት ክልል ይልካል፡፡ እንዲሁም የውጭ ዜጋ ለሆኑ ተመራማሪዎች የፓስፖርት ቁጥራቸውንና ዜግነታቸውን በመጥቀስ ለሚመለከተው አካል የይለፍ ፈቃድ እንዲያገኙ በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡
11. በአንቀጽ 21 የተቀመጡትን የባለስልጣን መ/ቤቱን የመስክ ተወካይ ተግባርና ኃላፊነት ይቆጣጠራል፡፡

## 20. በመስክ የሚካሄድ ጥናትና ምርምር ስራን የሚቆጣጠር ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

1. የመስክ ሥራው ባለሥልጣኑ በፈቀደው መሠረት የመንግሥትን ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፡፡
2. ጥናት ለሚካሄድበት ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ለሚመለከታቸው አካላት የሚጻፉ ደብዳቤዎችን መስክ ከመወጣቱ በፊት ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡ የተፈቀደውን የጥናት ቦታ የሚያሳዩ ካርታዎችና አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል፡፡ የጥናት ቦታው በተፈቀደው መሠረት መሆኑን አይቶ ያረጋግጣል፡፡
3. የመስክ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ከቡድን መሪው ጋር ሆኖ ስለሥራው ዓላማ የሚገልጽ የባለሥልጣኑን ደብዳቤ ጥናቱ በሚካሄድበት ክልል ወይም አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል ማቅረብና በመስክ ሥራ ወቅትም አስተዳደራዊ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
4. በመስክ ሥራ ወቅት ተመራማሪዎች ከአካባቢው ሕብረተሰብና ከአመራር አካላት ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት በአገናኝነት ይሰራል፡፡
5. የመስክ ጥናቱ አጥኝው ባቀረበውና ተገምግሞ በጸደቀው የጥናት ስልት መሰረት መካሄዱን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
6. በመስክ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ አጥኝዎች የሙያው ስነምግባር በሚፈቅደው መሰረት ጥናታቸውን እያካሄዱ መሆኑን ይከታተላል፡፡
7. የመስክ ሥራው ሂደት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ከቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት ጋር ግንኙነት በማድረግ ያሳውቃል፡፡
8. በመስክ ሥራ ወቅት ችግሮች ሲከሰቱ ወዲያው በአካባቢው ከሚገኙ የመንግሥት አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ ችግሩ መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ወዲያውኑ ለቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት በሚያመቸው መንገድ ያሳውቃል፡፡
9. በመስክ ሥራ ወቅት የተገኙ ግኝቶችን በሙሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ መግባታቸውን ማረጋገጥና ለግኝቶቹ ዝርዝር ካታሎግ ከተዘጋጀ በኋላ አመሳክሮ ለቅርስ ማሰባሰብ፣ማደራጀትና ላቦራቶሪ ዳይሬክቶሬት በማረካከብ ስለ አፈጻጸሙ መረጃ ይይዛል፤

FINAL DRAFT

10. የቅርስና የጂኦሎጂ ናሙናዎች ከመስክ ላይ ሲወሰዱ ይከታተላል፡፡ በተለይም ከመስክ ተሰብስበውና ታሽገው ወደ ብሔራዊ ሙዝየም የሚመጡና በላቦራቶሪ ውስጥ ብቻ ተከፍተው ጥናት ለሚካሄድባቸው የጂኦሎጂ ናሙናዎች ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

11. ከመስክ በተመለሰ በአምስት ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው የመስክ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት መሠረት የመስክ ሥራ ሪፖርት በሦስት ኮፒ አዘጋጅቶ ለቅርስ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

**ክፍል ዘጠኝ**
**ስለ ንብረቶች አገባብ፣ አያያዝና አጠቃቀም**

**21. የጥናትና ምርምር ንብረቶች አገባብ**

1. በጥናትና ምርምር ስም ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ንብረቶች አገባብ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ለጥናትና ምርምር ተግባር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የጥናት መገልገያ መሣሪያዎች በሀገሪቱ የጉምሩክ ደንብና አሰራር ይሆናል፡፡

**22. የጥናትና ምርምር ንብረቶች አያያዝ**

1. በፕሮጀክት ስም በባለሥልጣኑ አማካኝነት ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ንብረቶች አያያዝ የመንግሥትን ህግና ደንብ ተከትሎ ይሆናል፡፡
2. ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የገቡ የምርምር መሣሪያዎች ፕሮጀክቱና የባለሥልጣን መ/ቤቱ ንብረቶቹ እንዳይበላሹና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይንከባከባሉ፣ ከተበላሹም ያሰራሉ፡፡
3. በፕሮጀክት ስም ከቀረጥ ነፃ ለገቡ የምርምር መሣሪያዎች ዓመቱን ሙሉ የሚሸፍን የመድን ዋስትና ፕሮጀክቱ ይገባል፡፡

**23. የጥናትና ምርምር ንብረቶች አጠቃቀም**

1. ፕሮጀክቱ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማያከናውንበት ወቅት ባለሥልጣኑ መ/ቤት አስፈላጊውን ወጪ በመሸፈን በንብረቶቹ ይጠቀማል፡፡
2. የፈቃድ ዘመን ሲጠናቀቅ በፕሮጀክት ስም ከቀረጥ ነፃ የገቡ ንብረቶች የባለቤትነት መብት የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡
3. ፕሮጀክቱ ለመስክ ሥራ የሚገለገልባቸው ተሽከርካሪዎች በኪራይ ወይም የፕሮጀክቱ ንብረት ብሎ ያስመዘገባቸው ተሽከርካሪዎች ብቻ መሆን አለባቸው፡፡

FINAL DRAFT

<u>**ክፍል አስር**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

**24. ስለ ገቢ አጠቃቀም**

1. ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ከጥናትና ምርምር አገልግሎት የሚያገኘውን የጥናት ክፍያ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ተደርጎ ቅርሶች በተገቢው ሁኔታ ተጠብቀው የሚቀመጡባቸው ማሰባሰቢያ ቦታዎችን ለማስፋፋት፣ ቅርሶችን ለማደራጀት፣ ቅርሶችን ለመንከባከብና ለጥናት የሚያገለግሉ ሳይንሳዊ መሣሪያዎችን መግዣ እንዲሁም ጥናት ለሚካሄድባቸው ክልሎች ቅርስ ጥበቃ ጥናትና ልማት እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

**25. የመተባበር ግዴታ**

1. ማንኛውም ተመራማሪ ወይም በመስክ ላይ የተመደበ ባለሙያ ይህንን መመሪያ ሥራ ላይ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

**26. ቅጣት**

1. ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም አጥኚ ወይም የባለሥልጣኑ ባለሙያ ወይም ተወካይ አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

**27. ስለተሻረ መመሪያ**

1. በአርኪዎሎጂና አንትሮፖሎጂ መስክ ለሚካሄድ ጥናትና ምርምር ሐምሌ 12/1992 የወጣው የተሻሻለ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

**28. መመሪያውን ስለማሻሻል**

1. ይህን መመሪያ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሚኒስትሩ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**29፡ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

1. ይህ መመሪያ ከ___ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሚን አብዱልቃድር
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር
አዲስ አበባ

FINAL DRAFT